**March 13, 2019 QuickNotes**

**ለ MCPS የኣመቱ መምህር የመጨረሻ ዙር ሶስት ተወዳዳሪዎች ይፋ ተደረጉ**

በማርያን ግሪንብላት የትምህርት ገንዘብ ለሚደገፈው ለ2019–2020 የ MCPS የዓመቱ መምህር ሽልማት ሶስት መምህራን የመጨረሻ ዙር ተወዳዳሪዎች ተብለው ተሰየሙ። እነርሱም፦ **Maura Backenstoe**፣ በርኒንግ ትሪ አንደኛ ደረረጃ ት/ቤት (Burning Tree Elementary School) የሙዓለህፃናት መምህርት፣ **Madeline Hanington**፣ በሀለይ ዌልስ መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት (Hallie Wells Middle School) የእንግሊዝኛ ቋንቋ ስፔሻሊስት እና መምህርት እና **Teak Bassett**፣በክላርክስበርግ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Clarksburg High School) የማህበራዊ ጥናት መምህር ናቸው።

የግሪንብላት የትምህርት ፈንድ/Greenblatt Education Fund በተጨማሪም **Brendan Kelly** በአልበርት አንስታይን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Albert Einstein High School) የሙዚቃ መሣሪያ መምህር **Virginia Pantella** በጌትስበርግ መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት (Gaithersburg Middle School) የ STEM መምህር የሆኑትን የ2019 "Rising Star Teachers of the Year" የተሰኘ እውቅና ይሰጣል። ይህ ሽልማት ፈጠራዊነታቸውና ጉጉታቸው ተማሪዎች እንዲንጠራሩና/ራሳቸዉን እንዲያነሳሱ ተጨማሪ ግኝት እንዲያመጡ የሚያበረታታ ከኣምስት ኣመት በታች ተሞክሮ ያላቸውን መምህራን ያከብራል።

ለኣመታዊ መምህር ሽልማት የመጨረሻ ዙር ተወዳዳሪዎች፣ በ Montgomery County ኣምስት እመት ወይም ከዚያ በላይ የማስተማር ተሞክሮ እንዲኖራቸው የሚገባ፣ በመምህራን ቡድን፣ በትምህርት ቦርድ ኣባሎች፣ በ MCPS ሰራተኛ ኣባሎችና የ Montgomery County Council of PTAs ተወካዮች፣እንዲሁም በ Greenblatt የቤተሰብ ኣባላት ቃለ መጠይቅ ይደረግላቸዋል።

መምህራን፣ ከሌሎችም የ MCPS ሠራተኞች እና ኢጋሮች ጋር ስላበረከቱት አስደናቂ ሥራቸው የልጆች ሽልማት በአል/Children Awards Celebration አካል ዓመታዊ ሻምፒዮና በመሆን ይሸለማሉ። የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የዓመቱ መምህር/MCPS Teacher of the Year ሁነት የሚካሄደው ሐሙስ፣ ኤፕሪል 25 ጀርመንታወን/Germantown በሚገኘው ብላክሮክ የስነጥበብ ማዕከል (BlackRock Center for the Arts) ይሆናል።

የ Marian Greenblatt Fund፣ከቀድሞ የትምህርት ቦርድ ኣባል ስም የተሰየመ፣ ተማሪዎቻቸውን የግኝት ስሜት እንዲሰርፅባቸው ለሚያደርጉ መምህራን እውቅና ይሰጣል፣ ለልቀት እንዲጥሩ እና ት/ቤታቸውንና ማህበረሰባቸውን እንዲያግዙ ወጣት መምህራንን ያበረታታል። ድርጅቱ ለእያንዳንዱ የዓመቱ መምህር የመጨረሻ ዙር ተወዳዳሪ የ $2,000 ሽልማት፣ እና ለሁለቱ Rising Star Teaching ተሸላሚዎች ለእያንዳንዳቸው $1,000 ይሸልማል።

ለፍጻሜ ስለደረሱት የዓመቱ መምህር(ት)/(Teacher of the Year) የበለጠ ለማወቅ (ወደ ጋዜጣዊ መግለጫ አገናኝ )

**የሞንትጎመሪ ካውንቲ ስለ ዘር ፍትኃዊነት እና ማህበራዊ ፍትህ ላይ ያተኮረ ውይይት ያካሄዳል**

ረቡዕ ማርች 13፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ አስተዳደር የዘር እኩልነት እና ማህበራዊ ፍትኃዊነት ላይ የማህበረሰብ ውይይት ያካሄዳል። ሁነቱን የሚመሩት የካውንቲ ካውንስል ፕሬዚደንት Nancy Navarro እና የካውንቲ ሥራ አስፈጻሚ Marc Elrich ናቸው።

ካውንቲው ከነዋሪዎቹ ለመስማት ይፈልጋል። የዘር ፍትኃዊነት/እኩልነት ለምን አስፈላጊ ሆነ? በዘር መድሎአዊነት ተጽእኖ ደርሶብዎት ያውቃል? የዘር እኩልነትን እና ማህበራዊ ፍትህን ለማዳበር ምን አይነት ለውጦችን ለማየት ይፈልጋሉ?

ሁነቱ የሚጀመረው በ 7:30 p.m.  Silver Spring Civic Building, 1 Veterans Plaza ህንፃ ላይ ነው።

ጥያቄዎች ካሉዎት በስልክ ቁጥር፡- 240-777-7832 ደውለው ይጠይቁ።

[ተጨማሪ መረጃ]

**የቅድመ ሙዓለህፃናት/ሄድስታርት (Prekindergarten/Head Start) ምዝገባ እየተካሄደ ነው (እንግሊዝኛ እና ስፓንሽ)**

ለ 2019 - 2020 የትምህርት ዓመት በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ቅድመ ሙዓለህፃናት/MCPS (prekindergarten) ወይም ሄድስታርት (Head Start) ልጆቻቸውን ለማስመዝገብ የሚፈልጉ ወላጆች ከማርች 1 ጀምሮ ይችላሉ። የልጆች እድሜ ሴፕተምበር 1/2019 ወይም ቀደም ብሎ 4 አመት መሙላት አለበት፣ ወላጆችም የገቢ መስፈርት ማሟላት ይኖርባቸዋል። ስለ ብቃት መመሪያ፣ ቦታ እና የማህበረሰብ መመዝገቢያ ጊዜያት ወይም ማመልከቻ የተሟላ ለማድረግ ስለሚያስፈልጉ ማስረጃዎች/ሠነዶች የበለጠ መረጃ/ኢንፎርሜሽን ለማግኘት በስልክ ቁጥር፡- 240-740-4530 ይጠይቁ።

**የ MCPS Summer RISE ተቀባይ ለመሆን አሁን ያመልክቱ**

ጥሪ ለሁሉም የሞንትጎመሪ ካውንቲ የቢዝነስ፣ የመንግስት ኤጀንሲዎች፣ እና ትርፍማ ያልሆኑ ድርጅቶች! ለ 2019 Summer RISE program አሁን ለምዝገባ ክፍት ነው!
ሠመር ራይዝ/Summer RISE በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ጁንየሮች እና ሲንየሮች በሙያ ላይ የተመሠረተ ትምህርት እና ልምዶችን ይሰጣቸዋል፤ እና ቀጣሪዎች በችሎታ/ዝንባሌ ላይ ትኩረት ሰጥተው ለመኮትኮት ይረዳቸዋል። Summer RISE ትምህርትን የመቅሰም እድሎችን ይሰጣል እናም ተማሪዎችን ከሙያ ምርጫዎች ጋር ያስተዋውቃል። ስለ Summer RISE የበለጠ መረጃ ለማግኘት እና ለተቀባይነት ምዝገባ ይህንን ድረ-ገጽ ይጎብኙ www.MCPS-SummerRISE.org።

**የ 2017 - 2018 የትምህርት ዓመት ዓመታዊ ሪፖርት**
የ2018 ለማህበረሰብ የተዘጋጀ ዓመታዊ ሪፖርት አሁን ይገኛል። ለማህበረሰብ የቀረበ ዓመታዊ ሪፖርት ከ2017 - 2018 የትምህርት ዓመት ትኩረቶች እና በዲስትሪክቱ ውስጥ ለውጥን የሚገፋፉ እውነታዎችን ይዳስሳል። ሪፖርቱ፡- ስለማንነታችን፣ ስለተማሪዎች አፈፃፀም መረጃ፣ የሥራ ሂደት መረጃ፣ እና የ MCPS ን ራእይ እና ተልእኮ ለመፈጸም MCPS የወሰዳቸውን እርምጃዎች ለማህበረሰቡ መረጃዎችን/ኢንፎርሜሽን ይሰጣል። ዓመታዊ ሪፖርቱን ለማየት
[ይህንን ድረ-ገጽ] ይጎብኙ።

**የመጨረሻ ጥሪ፦ "Design Your Dream Classroom" የተሰኘ ውድድር ማስገቢያ ማርች 15 ይጠናቀቃል**
ስለ ዘንድሮው "United We Learn" ስለ ወደፊት ትምህርት ቤቶች የውድድር ማስገቢያ የሚቀረው ጊዜ አራት ሣምንት ያክል ነው።

የዚህ ዓመቱ ውድድር ተማሪዎች የራሳቸውን ሁነኛ ነው ብለው የሚያልሙትን የመማሪያ ቦታ ንድፍ እንዲያዘጋጁ እና ግኡዙ አካባቢያቸው በመማር ችሎታቸው ላይ ስለሚያሳድርባቸው ተጽእኖ በአንክሮ እንዲያስቡ/እንዲጋፈጡት ያደርጋቸዋል።

ውድድሩ የሚካሄደው ተማሪዎች እና ሠራተኞች በትምህርት ቤታቸው የመማሪያ ቦታዎችን እንዴት እንደሚጠቀሙ እና የወደፊት መማሪያ ክፍሎቻቸውና ትምህርት ቤቶች ምን መምሰል እንዳለባቸው የተጠየቁበትን የኖቬምበር 2018 የዳሰሳ ጥናት ተከትሎ ነው። በዳሰሳ ጥናቱ ግብረ መልስ ላይ በተደጋጋሚ የተጠቀሱ መሠረታዊ ነገሮች፤ ስለ ከለር/ቀለም፣ ብርሃን፣ አስፈላጊ መሣሪያዎች/እቃዎች/furniture፣ ቴክኖሎጂ እና ደህንነት/security ከግምት ዉስጥ ተካተዋል። የትምህርት ተቋማቶቻችንን ቀጣይነት ባለው መልኩ ለማሻሻል/ለማዳበር ግብረመልሱ ይጠቅማል። ውድድሩ ተማሪዎች የወደፊት መማሪያ ቦታቸው ምን መምሰል እንዳለበት ራዕያቸዉን ሲነድፉ እነዚህን ተመሳሳይ ነገሮች ግንዛቤ ዉስጥ እንዲያስገቡ ያደርጋቸዋል። ተማሪዎች በዚህ ውድድር ላይ በመሣተፍ የወደፊት የተሻለ ንድፍ እንዲኖር ተጽእኖ የማድረግ ችሎታ ሊኖራቸው ይችላል። **የማቅረቢያው ጊዜ ዓርብ፣ ማርች 15 ነው።**

የበለጠ ዝርዝር መረጃ በውድድሩ ድረ-ገጽ ላይ ይገኛል።

ይህንን ቪድዮ ይመልከቱ የበለጠ መረጃ ለማግኘት

**የትምህርት ቦርድ በስነ-ምግባር ጓድ/Ethics Panel ኣንድ ክፍት ቦታ ለመሙላት ኣመልካቾች ይፈልጋል**
የ Montgomery County የትምህርት ቦርድ ለባለ ኣምስት ኣባል የEthics Panel (የስነ-ምግባር ጓድ) ኣንድ ክፍት ቦታ ለመሙላት ይፈልጋል። ክፍት ቦታው ከጁላይ 1፣ 2019 ጀምሮ ለሶስት ኣመት የኣገልግሎት ጊዜ ነው። ኣባላት በነፃ ነው የሚያገለግሉት።

የፓናል አባላት በዚህ ወቅት የትምህርት ቦርድ አባል፣ የትምህርት ቤት ኃላፊዎች፣ሠራተኞች ወይም ለትምህርት ቦርድ ተጠሪነት ያለው የቢዝነስ ድርጅት ተቀጣሪ ሰዎች፣ ወይም የእንደዚህ ዓይነት ግለሰቦች የትዳር አጋርነት ያላቸው አይሆኑም። ጓዱ/ቡድኑ በአመት አንድ ጊዜ በመገናኘት የፋይናንስ መግለጫ ፎርሞችን ድህረ እይታ ያደርጋል እንዳስፈላጊነቱም የምክር አስተያየት ቅሬታዎችንና ጥያቄዎችን ይገመግማል። በጁን በሚደረገዉ የትምህርት ቦርድ ስብሰባ ላይ ለሚሆነዉ ስያሜ/ምደባ፣ አመልካቾች ሰኞ ሜይ 13/2019 5:00 p.m. ረዙሜ (resumé ) ወይም ማመልከቻቸውን የሚደግፍ ሌላ ማስረጃ ፍላጎታቸውን ከሚገልጽ ደብዳቤ ጋር ማቅረብ ይኖርባቸዋል።

የበለጠ መረጃ ድረ-ገጽ ላይ ይገኛል።